# የሞተን አትርሳ የወደቀን አንሳ!

# ሳሙኤልም እንደ እስጢፋኖስ!

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

ምእራባውያን፣ አረቦችችና ሱዳን እንደ እንደ ባቄላ ፉል ቀቅለው ያበሰሉት ህወሀት እንደ ቂጣ ጠፍጥፎ የሰራቸው ሎሌዎች አዲሳባ፣ ባህርዳር፣ ናዝሬትና አዋሳ ተወንበር ቁጢጥ እስታሉበት ጌዜ ድረስ አያሌ በውጪ ያሉ የኢትዮጵያውያን ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ዌብ ሳይቶችና የሐሳብ አምዶች፤ ራዲዮኖችና ቴሌቪዥኖች "ነፃ ሚዲያ ነን" እያሉ ይደሰኩሩ ነበር፡፡

እነዚህ ነፃ ሚዲያ ነን ባዮችም በበደኖ ገደል የተጣሉትን፣ በጋንቤላ ተመስክ የተረፈረፉትንና በኦጋዴን ተአሸዋ የተጎተቱትን እስከሬኖች ነጋ ጠባ ለሕዝብ እያደረሱ ሰማእታትን ዘካሪ ይመስሉ ነበር፡፡ አጋዚ በዘጠና ሰባቱ ምርጫ ሰበብ በህዳርና በሰኔ የጨረገዳቸውን ወገኖቻችንን ለማስታወስ ፎቶግራፎቻቸውን ተሚበራ ሻማ ጋር እያከታተሉ እየለጠፉ ጀግና አስተዋሽ ይመስሉ ነበር፡፡ በአምባ ጊዮርጊስ በአጋዚ ጥይት የቆሰሉትን ህፃናት፣ በባህርዳር በስናፐር የረገፉትን ወጣቶች፣ በወልዲያ በቃና ዘገሊላ የረገፉትን እነ ዮሴፍን እየዘገቡ አደራቸውን የተወጡ ይመስሉ ነበር፡፡ በኦጋዴን የወንድሙን ሬሳ እንዲጎትት፣ ወለጋም እናቱን ገድለው በእናቱ ሬሳ እንዲቀመጥ የታዘዘውን ልጅ ደጋግመው እያነሱ ኢሰብአዊ ድርጊት እንቅልፍ የሚነሳቸው ይመስሉ ነበር፡፡ በወህኒ የተገረፉትን፣ ተመንገድ የወደቁትን፣ የተሰደዱትን፣ የተራቡትን፣ የተጠሙትን ሁሉ እያሳያዩ ግዴታቸውን የተወጡ ይመስል ነበር፡፡

ህወሀት የተባለው ባንዳ ለጊዜው ገሸሽ ብሎ የህወሀት አሽከር ባንዳዎች ተወንበር ሲወዘፉ ከጥቂቶች በስተቀር "ነፃ ሚዲያ ነን" ሌላ ጊዜም "የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ነን" እያሉ ሲደደኩሩ የኖሩት ሁሉ የእነዚህ አሽከር ባንዳዎች አገልጋይ ሆኑና ጭምብላቸውን ገልጠውት አረፉ፡፡ ተህወሀት አሽከሮች ተጋብተው የፖለቲካ ንግድ ሲነግዱባቸው የኖሩትን ጀኖች ሰማእታት ዘነጉ፡፡ ብአዴን፣ ኦዴፓ ቅብጥሶ ለሚባሉት የህወሀት አሽከሮች ራሳቸውን ድረው የዶሮ ፍትፍቷን ውጣ እንደ እምትፍነከነክ ሙሽራ ጫጉላ ውስጥ እየተሽኮረመሙ በይህ አድግ ባሩድና ብትር ላለፉት ሰላሳ ዓመታት የረገፉትን

ሰማእቶች ብቻ ሳይሆን በአሁኑ ሰዓት የዘር ፍጅት ሰለባ የሆኑትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስደኞችና ሰማእቶችንም ማንሳት አይፈልጉ፡፡

ሰማእታትን መዘንጋት አድራን መብላት ነው፡፡ አደራን መብላትም እርምን መብላት ነው፡፡ እርምን መብላትም መረገም ነው፡፡እርማችንን እየዋጥን የሰማእታትን ነፍስ እንደ ትንኝ ነፍስ ቆጥረን "ያለፈውን በይቅርታ መላፍ በሚል!" የሆዳምና የአረመኔ ፈሊጥ እኛ ከርሳችንን ስንቆዝር ለፍትህ ከተሰውት መቃብር ቆመን የወደፊት እንጀራችንን ለመገጋር የምንቋምጥ የትዬለኔ ነን፡፡ ለእነዚህ እርማቸውን ከበላነውና ነፍሶቻቸው ፍትህን በመጠበቅ ላይ ካሉት ሰማእታት መካከል ለእኛ ሲል እንደ እስጢፋኖስ ተቀጥቅጦ የተገደለው የሕዝብ ጠበቃው ሳሙኤል አወቀ አንዱ ነው፡፡

ሰማእቱ ሳሙኤል አወቀ ተሰውቶ ፍትህን ሳያገኝ ስድስት ዓመታት አለፉት፡፡ ሳሙኤል




ሮጦ ሳይጠግብ ያለፈ ሰማእት ነው፡፡ እንደ ሌሎች ሰማእታት ሳሙኤል የተሰዋው ግፉዓንን ከግፍ ቀንበር ለማላቀቅ ሲጥር ነው፡፡ ሳሙኤል የተሰዋው እንደ ጳጳሳት ከግፈኞች ጀርባ ማረጥረጥ፣ እንደ ልማታዊ ሐኪሞች ከገዳዮች ጋር መዳራት፣ እንደ ምሁራን ተብዮዎች አድርባይነትን ተከናንቦ ህሊናውን መግፈፍ ተስኖት ነው፡፡ ለግፉዓን ራስን አሳልፎ መስጠት ቅድስናና ብጽእና ነው፡፡ ቅድስናንና ብጽእናን የሚቀልቧቸው ምዕመናን ሲረሽኑ ለማይተነፍሱ እንዲያውም ከረሻኙ ጀርባ ለሚቆሙ አቡንና ጳጳሳት እየሰጡ ብጹእ ቅዱስ ማትያስ፣ ብጹእ ቅዱስ ገብርኤል፣ ብጹእ ቅዱስ ፋኑኤል ወዘተርፈ እያሉ መጥራት በእምነት ማፌዝ ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን ታሪኮችም ሆነ ገድሎች እርግጠኝነት የሚጠራጠር በጦቢያ የሚፈጸሙትን ሰቀቃዎች በጥሞና ቢመለከት በቅዱሱ መጽሐፍ የተመዘገቡ የቅዱሳትን ተጋድሎና የደረስባቸውን ግፍ ወደ ማመን ይጠጋል ብዬ እገምታለሁ፡፡

እንደሚታወቀው እስጢፋኖስ ለእምነቱ ሲል በድንጋይ ተወግሮ የሞተ ክርስቲያን ነው፡፡ እስጢፋኖስ ልቡን ለሚያምንበት ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ሰጥቶ በርትዑ አንደብቱ ስለክርስቶስ ሲሰብክ ከሀዲና ቀጣፊ ፈሪሳውያን *"በሙሴ ላይ፤ በእግዚአብሔርም ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተዋል የሚሉ ሰዎች አስነሱ ፡፡ ሕዝቡንና ሽማግሌዎችንም፣*

*ጻፎችንም፤ አናደዱ፤ ቀርበውም ያዙት፣ ወደ ሸንጎም አመጡትና ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም፣ ይህ የናዝሬቱ እየሱስ ይህንን ሥፍራ ያፈርሰዋል፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋል የሚሉ የሐሰት ምስክሮች አቆሙ፡፡፡"* ሐዋ ሥራ ፮፡ ፲፫-፲፬

ሶፋ ላይ ተንፈላሶ ቁርጡን እየቆረጠ ወይም ውስኪውን እየጨለጠ "አርፎ አይቀመጥም" ለሚል የኔ ቢጤው ክብር የለሽ አሳማ ወይም ቅንቡርስ እንደ ሰማእት ላይታይ ቢችልም ሳሙኤል አወቀም እንደ እስጢፋኖስ ለሚያምንበት ተወግሮ የተሰዋ ጀግና ነው፡፡ ሳሙኤል ልቡን ለሀገሩና ለነፃነቱ ሰጥቶ በርትዑ አንደበቱ ስለ አገሩ፣ ስለፍትህንና ነፃነት ሲሰብክ የበፊቶቹ ፈሪሳውያን በእስጢፋኖስ ላይ *"ሙሴንና እግዚአብሔርን ሰድቧል፣ ሙሴ ያስተላለፈልንን ሕግን ይለውጣል"* የሚሉ ስም አጥፊ ሰባኪዎች እንዳሰማሩበት የዛሬዎቹ ፈሪሳውያንም "ሳሙኤል አወቀ ሰላምን ያናውጣል፣ ሽብርን ይነዛል፣ ሕገ-መንግስትን ይንዳል" የሚሉ ቀጣፊ ካድሬዎችን አሰማሩበት፡፡ ሕዝብ ግን እውነተኛውን እስጢፋኖስ በተመስጦ እንዳዳመጠው ሁሉ ባለማተቡን ሳሙኤልንም በጥሞና ያዳምጥ ነበር፡፡

እስጢፋኖስ የኦሪትን ሕግና የነባያትን መጻሕፍት እየጠቀሰ ቢያስረዳቸውም ፈሪሳውያን አልሰማ ስላሉት "*እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁም ጆሯችሁም ያልተገረዘ እናንተ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንደ ተቃወሙት እናንተ ደግሞ፡፡ ከነብያትስ አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማን ነው? የጻድቁን መምጣት አስቀድመው የተናገሩትን ገደሏቸው፤ በመላእክት ሥርዓት ሕግን ተቀብላችሁ ያልጠበቃችሁት እናንተም አሁን እርሱን አሳልፋችሁ ሰጣችሁ፡ ገደላችሁትም፡፡*" አላቸው፡፡

ሳሙኤል አወቀም በሐሳብ ክርክርና በህሊና መኖር የማያምኑትን ጭራቅ አሳዳጆቹ ስላልሰሙት " *እናንተ የሰውነትም ሆነ የመንግስትነት ባህሪ የሌላችሁ በድንቁርና ልባችሁን ያደነደናችሁ እውነትን፣ ፍትህንና ነጻነትን ትቃወማላችሁ፤ ባንዳ አባቶቻችሁ ከጠላት አብረው የጦቢያን አርበኞች እንዳሳደዱት፤ እናንተም የሞሶሎኒን ሐውልት ስንቃወም፣ የአርበኞቻችንና የሰማእቶቻችንን ቀን ስናከብር ታሳድዱናላችሁ፡፡ በአገር ውስጥ በግፍ የታሰሩት ወገኖቻችን እንዲፈቱ፤ በውጭም ዜጎቻችን ተከብረው እንዲኖሩ ስንጠይቅ ወህኒ ትከቱናላችሁ፡፡ ሕገ-መንግስት የሚል ቃል እያነበነባችሁ እናንተ ግን ሕግን እየጣሳችሁ በሕገ- አራዊት ትኖራላችሁ*" አላቸው፡፡

በእስጢፋኖስና በሌሎችም ሐዋርያት ትምህርት የክርስትና ተከታዮች ቁጥር እጅግ እየበረከተ መጣ፡፡ ይህንን የክርስትና ተከታዮችን መብዛትና የእስጢፋኖስንም እውነተኛነትና ቁርጠኝነት የተመለከቱ ፈሪሳውያን ቀኑ፤ ተበሳጩ፡፡ *"የተበሳጩት ፈሪሳውያን በልባቸው በጣም ተቆጡ፣ ጥርሳቸውንም አፋጩበት፡፡ በታላቅ ድምጽም እየጮሁ ጆሯቸውን ደፈኑ፣ በአንድ ልብ ሆነውም ወደ እርሱ እሮጡ፤ ከከተማም ወደ ዉጪ አውጥተው ወገሩት፡፡ ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በሚሉት በአንድ ጎብዝ እግር አጠገብ አኖሩ፡፡ እሲጥፋኖስም ጌታ እየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር፡፡ ተንበርክኮ ጌታ ሆይ ይህንን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ፡፡ ይህንንም ብሎ አንቀላፋ፡፡ ሳውልም በእርሱ መገደል ተስማምቶ ነበር፡፡ "* የሐዋ *ሥራ* ፯፥፶፬-፶፰.

እንደ እስጢፋኖስ የእምነት ተከታዮች ሁሉ የሳሙኤል ተከታዮች ቁጥርም እየበዛ መጣ፡፡ ይህንን የሳሙኤል ተከታዮች መብዛት፣ የሳሙኤልን እውነተኝነትና ቁርጠኝነት የተመለከቱ ፈሪሳውያን እጅግ  ተበሳጩ፡፡ ጥርሳቸውምንም እያፋጩ ዛቱበት፣ ከስራ አባረሩት፣ በግሉ ሰርቶ እንዳይበላ ከለከሉት፣ አሰሩት፣ ገረፉት፣ አገሩን ጥሎ እንዲሸሽም አስጠነቀቁት፡፡ ሳሙኤልም *"የምከፍለው ዋጋ ለሀገሬና ለነፃነት ነው፤ ከታሰርኩም ኀሊናዬ አይታሰርም፤ ከገደሉኝም ትግሌን አደራ! በተለይ የኔ ትውልድ አደራ!!!"* ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ፡፡ ፈሪሳውያንም በአንድ ልብ ሆነው ወደ እርሱ እሮጡ፤ ከመነሐሪያ ወደ ውጪ አውጥተውም ወገሩት፡፡ ሳሙኤልንም ይህችን ግፍ እንደ ዶፍ የሚወርድባት ምድር ለመልቀቅ ሽልብ አለ፡፡ በሳሙኤል መወገር የተሰማሙት ሰዎች ቁጥርም ሆነ ሳሙኤል በሚወገርበት ሰዓት የተናገረው ለጊዜው አይታወቅም፡፡ እውነቱ ተመርምሮ ዘግይቶ እንደተጻፈው የእስጢፋኖስ ገድል የሳሙኤል ገድልም ተመርምሮ ዘግይቶ ይጻፋል፡፡

እስጢፋኖስ ተወግሮ ቢሞትም የሞተለት ክርስትና በምድር ተስፋፍቷል፡፡ ከአጠገቡ ቆሞ ያስቀጠቀጠው ሳውልም ንስሃ ገብቶ ክርስትናን አስፋፍቷል፤ ክርስትናን በመስበኩም አንገቱን ተቀልቷል፡፡ በዚህ ግብሩም ቅዱስ ጳውሎስ ተብሏል፡፡ እንደ እስጢፋኖስ ሳሙኤልም ለእምነቱ ተወግሮ ቢሞትም የሞተለት የነፃነትና የፍትህ እምነት ይስፋፋል፡፡ ተቀናቃኙ ስንታየሁ ወልደሚካኤልም ከነፍሰ-ገዳዮች ፓርላማ እንደ ድንጋይ መጎለቱን ትቶ ንስሃ በመግባት ሳሙኤል ለተሰዋለት የነፃነትና ፍትህ እምነት አንገቱ እስከሚቀላ እንደሚሰብክ እስካሁን ይጠበቃል፡፡ ከሶስት ዓመታት ወዲህ ከሳሙኤል ገዳይ ድርጅት

ጋር ቀለበትና ሰርግ የፈጠሙት የድሮ የሳሙኤል የትግል ጓዶችም ንስሐ ገብተው ለሳሙኤል ፍትህን እንዲጠይቁ የሰማእቱ ደሞ ይጮኻል፡፡

በክርስትና ታሪክ እስጢፋኖስ በሰማእትነቱ እንደሚዘከረው ሁሉ በኢትዮጵያ የሀገር፣ የነፃነትና የፍትህ ታሪክም ሳሙኤል ሲዘከር ይኖራል፡፡ እስጢፋኖስን የገደሉትና የከደዱት እርኩሶች በሰማይና በምድር ሲረገሙ እንደሚኖሩት ሁሉ ሳሙኤልን የገደሉትና የከዱት እርኩሶችም በምድር ስማቸውና ስጋቸው በሰማይም ነፍሳቸው ሲቃጠል ይኖራል፡፡ እስጢፋኖስን ለማዳን ያልጣሩት አድር ባዮች ስም የለሽ ሆነው እንደ ቀሩት ሁሉ ሳሙኤልን ለማዳን ያልጣርን አድር ባዮችም ስማችን ሳይጠራ ይኖራል፡፡ ከእስጢፋኖስ ገዳዮች ጋር ሲሞዳሞዱ የነበሩት ከርሳሞች ሲረገሙ እንደሚኖሩት ሳሙኤልን ካስገደሉት ጋር በጥቅም ምላስ የምንሞዳሞድና ክብራችንን ጥለን ደጅ የምንጠናም ሥጋችን ሲበጨቅ፣ ነፍሳችንም ሲረገም ይኖራል፡፡

በኤፍሬም ይሳቃዊ ወስላታ "አገራዊ እርቅ" እያሳበብን ፍትህን ረግጠን በእነሳሙኤል አወቀ መቃብር ላይ እንጀራችንን ከመጋገር መለኮት ይጠብቀን፡፡

ባለማተቡን ሳሙኤልን አሳድገው ለአገር ያበረከቱ ወላጆች ታላቅ ክብር ይገባቸዋል፡፡

እንደ እስጢፋኖስ ተወግሮ የተገደለውን የሳሙኤልን ነፍስ ይማር፡፡

የሞተን አትርሳ የወደቀን አንሳ ነውና ምን ጊዜም ሰማእታትን አንርሳ!

*መጀመርያ ሰኔ ሁለት ሺ ሰባት ዓ.ም. ከዚያ በኋላም በየዓመቱ መታተም ቀጠለ፡፡*